# የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት

# ደቡብ ኢትዮጵያ ነጋሪት ጋዜጣ

# DEBUB ETHIOPIA NEGARIT GAZETA

# OF THE SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE

፪ኛ ዓመት ቁጥር42
አርባ ምንጭ ታህሳስ 5ቀን ፪ሺ፲፮ዓ.ም

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት
ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No 42
Arba minch December. 2023

**አዋጅ ቁጥር ፳፫ /፪ሺ፲፮ ዓ.ም**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት የቴምብር ቀረጥ አዋጅ**

**መግቢያ**

በክልሉ የቴምበር ቀርጥ አከፋፈል ስርዓት በፌዴራል መንግሥት ከፀደቀው የቴምበር ቀረጥ አዋጅ ጋር ተጣጥሞ መደንገግ እንዳለበት በመታመኑ፣

በሰነዶች ላይ የተጣለውን የቴምበር ቀረጥ የኪነ ጥበብ እድገትና የካፒታል እድገት ዝውውርን ለማገዝ በሚያስችል አኳኋን መደንገግ በማስፈለጉ፣

የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምክር ቤት በክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ 3(1)/ሀ/ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ **"የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የቴምብር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 23/2016"** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) **"ቢሮ"** ማለት የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ገቢዎች ቢሮ እና እንደአግባብነቱ በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ መምሪያዎች፤ ጽ/ቤቶች እና የታክስ ማዕከላትን ይጨምራል፤

**Proclamation 23/2023**

**SOUTH ETHIOPIA REGIONAL STATE STAMP DUTY PROCLAMTION**

**Preamble**

**Whereas**, it is necessary that the stamp duty payment system in the region shall be consistent with the Stamp Duty Proclamation approved by the Federal Government;

**Whereas,** it has become necessary to levy the stamp duty on documents in a manner which would contribute to the development of art, and the transfer of capital assets;

**Now, Therefore,** the South Ethiopia Regional State Council has issued this proclamation in accordance with Article 54 sub Article 3(1) /a/ of the constitution of the Region.

**SECTION ONE**

**GENERAL**

**1. Short Title**

This proclamation may be cited as **"the stamp duty proclamation of South Ethiopia Regional State Proclamation No.23/2023"**

**2. Definitions**

Unless the context requires otherwise, in this proclamation:

1) **"Bureau"** means the Revenue Bureau of the South Ethiopia Region as well as the departments and office at each administrative level;

| | |
|---|---|
| 2) **“ግልግል”** ማለት ስለ ግልግል፣ስለ እርቅ፣ ስለስምምነት ወይም ስለሌላ ተመሳሳይ ጉዳይ በሁለት ተዋዋይ ወገኖች በተደረገ ስምምነት መሠረት በፍርድ ቤት ሳይሆን በገላጋዮች አልቆ በፁሑፍ የተሰጠ ውሳኔ ነው፤ | 2) **“Award”** means a decision in writing rendered by an arbitrator/s/ on reference made otherwise than by order of Court in the course of Suit by parties to a Compromise, Conciliation or arbitral submission or other similar matters; |
| 3) **“ማገቻ”** የተወሰነ ነገር በመፈጸሙ ወይም ባለመፈጸሙ ምክንያት የሚቀር ሆኖ፣ አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበት ማናቸውንም ሰነድ ወይም በምስክር የተረጋገጠ ሆኖ ነገር ግን በትዕዛዝም ሆነ ለአስመጭው የማይከፈልበት አንድ ሰው ለሌላው ገንዘብ ለመክፈል ግዴታ የሚገባበትን ማናቸውም ሰነድ ይጨምራል፤ | 3) **“Bond”** includes any instrument, where by a person obliges himself to pay money to another, on condition that the obligation shall be void, if a specific act is performed or is not performed, as the case may be: or any instrument attested to by a witness and not payables to order or bearer, where by a person obliges himself to pay money to another; |
| 4) **“የህብረት ስምምነት”** በአንድ ወይም ከአንድ የሚበልጡ የሠራተኞች ማሕበራት ወኪሎች እና በአንድ ወይም ከአንድ የሚበልጡ አሰሪዎች ወይም የአሰሪ ማሕበራት ወኪሎች ወይም አሰሪዎችን በሚወክሉ ተጠሪዎች መካከል ስለ ሥራ ሁኔታዎች የሚደረግ በጹሑፍ የሰፈረ ስምምነት ነው፤ | 4) **“Collective Agreement”** means an agreement relating to Conditions of work, Concluded in writing and one or more employers or agents or representatives of employers, organizations; |
| 5) **“የሥራ ውል”** ማለት ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው በአሰሪ መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ ለአሰሪው ለመስራት ሲስማማ በሁለቱ መካከል የሚመሠረት ውል ነው፤ | 5) **“Contract of Employment”** means an agreement formed where a person agrees, directly or indirectly to perform, work for a definite or indefinite period or, piece of work in return for remuneration; |
| 6) **“ሰነድ”** ማለት ማንኛውም መብት ወይም ግዴታ የተመሰረተበት፣ የተመዘገበበት፣ የተላለፈበት፣ የተወገደበት፣ ልኩ የተወሰነበት ፣ ወይም የተስፋፋበት ወይም የተጠቀሰው ድርጊት ተፈጽሟል የተባለበት ማንኛውም የጹሑፍ ማስረጃ ነው፤ | 6) **“Instrument”** means a written document by which any right or obligation is or purports to be created, recorded, transferred, extinguished or by which its scope is limited or extended; |
| 7) **“ማረጋገጫ”** ማለት የህዝብ ጉዳዮችን ለማረጋገጥ ሥልጣን ባለው ሰው በሰነዶች ላይ የሚሰጥ ምስክርነት ነው፤ | 7) **“ Notaries Act”** Means an act of attestation and certification performed by person/s/ authorized to perform such acts; |
| 8) **“ሰነድ ማስፈጸም”** ማለት ሰነድ መስራት ማውጣት በሰነዱ የተመለከተውን ማስፈጸም ወይም ሰነዱን | 8) **“To Execute Instrument”** Means to draw, issue, to cay into effect or to negotiate an instrument; |

| | |
|---|---|
| ማዛወር ነው፤ | |
| 9) **“የመያዣ ሰነድ”** ማለት በተበዳሪው ወይም ዋሱ ለአበዳሪው በሙሉ ወይም በከፊል ንብረቱን በመያዣነት የሚሰጥበት ሰነድ ነው ፤ | 9) **“Security Deed”** Means any Instrument Where by a borrower or guarantor gives to a lender a charge upon a part or the Whole of this property; |
| 10) **“የመተዳደሪያ ደንብ”** ማለት እንደአግባብነቱ የመመስረቻ ጹሑፍን ይጨምራል፤ | 10) **“Articles of Association”** include Memorandum of association; |
| 11) **“ሰው”** ማለት ማናቸውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ማናቸውም ሰው ነው:: | 11) **“Person”** means any natural person or juridical person; |
| **ክፍል ሁለት** | **SECTION TWO** |
| **ስለ ቴምብር ቀረጥ አከፋፈልና አተማመን** | **Chargeable and assessment of Stamp duty** |
| **3. የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሰነዶች** | 3**. Instruments Chargeable with Stamp Duty** |
| 1) የሚከተሉት ሰነዶች የቴምብር ቀረጥ ይከፈልባቸዋል:: | 1) The following instrument shall be chargeable with stamp duty; |
| ሀ/ የማንኛውም የንግድ ማሕበር፣ የኀብረት ሥራ ማሕበር ወይም የማንኛውም ዓይነት ማሕበር መመስረቻ ጹሑፍ መተዳደሪያ ደንብ | a/ Memorandum and articles of association of any business organization, cooperative or any other form of association; |
| ለ/ ግልግል | b/ award; |
| ሐ/ ማገቻ | c/ bonds; |
| መ/ የዕቃ ማከማቻ | d/ warehouse bond; |
| ሠ/ ውል፣ ስምምነትና የነዚህ መገለጫዎች | e/ Contract and agreements and memoranda there of; |
| ረ/ የመያዣ ሰነዶች | f/ Security deeds; |
| ሰ/ የሕብረት ስምምነት | g/ Collective agreement; |
| ሸ/ የሥራ/ቅጥር/ ውል | h/ Contract of employment; |
| ቀ/ የኪራይ የተከራይ አከራይና መሰል መብት የማስተላለፊያ ሰነዶች ጭምር | i/ Lease; including sub-lease and transferee of similar rights; |
| በ/ ማረጋገጫ | j/ notarial acts; |
| ተ/ የውክልና ሥልጣን | k/ Power of attorney; |
| ቸ/ የንብረት ባለቤትነት ማስመዝገቢያ ሰነድ | |
| ነ/ በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ሀብት የሚወርሱ | |

**ወራሾች የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ዋጋ ላይ 1% ብቻ ይሆናል፡፡**

**ኘ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ነ የተደነገገው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ወራሾች በሞግዚት እንዲተዳደር ሆኖ ከቆዩ በኂላ ወራሾች የድርሻቸውን ንብረት ሲከፋፈሉ ከአሁን በፊት ለስመ ንብረት ዝውውር የከፈሉበት ማስረጃ ከቀረበ በድጋሜ የቴምብር ቀረጥ አይጠየቅበትም፡፡**

**አ/ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የግለሰብ ስም መጠሪያ በፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲቀየር ከተደረገ እና በህግ አስገዳጅነት የግለሰብ መጠሪያ ስሙ መቀየሩን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ ከተቻለ የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ዋጋ ላይ 1% ብቻ ይሆናል፡፡**

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ ቁጥር (ቸ) ስር የሰፈረው ድንጋጌ ቢኖርም በሞት ወይም በሌሎች የፍቺ ምክንያቶች የሁለቱ ተጋቢዎች የጋራ ሀብት የሆነ ማናቸውም የሚንቀሳቀስ ወይም የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ከአንደኛው ተጋቢ ወደ ሌላኛው ስም በሚተላለፍበት ጊዜ ለሚፈፀም የስመ-ንብረት ዝውውር የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም፡፡

**4.የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል**

1) በአንቀጽ 3 ስር በተመለከተው በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ መከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዚህ አዋጅ አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ ውስጥ እንደተዘረዘረው ይሆናል፡፡
2) አንድ ሰነድ በተደጋጋሚ ተፈጻሚ ሲሆን ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው ነው፡፡

l/ documents of title to property

m/ According to the court decision, the stamp duty will be only 1% on the value of property title registration for heirs inheriting wealth.

n/ Subject to the provisions stipulated in –paragraph 13 of this article, after the heirs who have not reached the age of majority have been managed by guardian ,when the heirs divide their property, stamp duty will not be charged again.

o/ If an individual´s name is charged by a court decision due to force majeure, and if it is possible to provide proof that the individual´s name has been changed, the stump duty will be only 1% on the value of property ownership registration.

2) Notwithstanding sub article (1) letter /i/ of this Article, no stamp duty is payable on transfer of title on the ownership of any movable or immovable property ,joint property of the two spouses, due to death or any other reasons of divorce.

**4. Rates of stamp duty**

1) The rate of tax payable on each document referred to in Article 3 shall be as set out in the
2) When a document is repeatedly applied, the amount of tax to be paid is as indicated in the table annexed to this Proclamation.

| | |
|---|---|
| 5. **የቴምብር ቀረጥ አተማመን** | **5. Mode of Valuation** |
| 1) በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የሚችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ላይ የሚከፈለው የቀረጥ መጠን በሠንጠረዥ ላይ እንደተመለከተው የዋጋው መቶኛ ይሆናል፡፡ | 1) Where the value of the right or obligation executed by means of an instrument can be determined the rate chargeable on such instrument shall be the percentage of such value as specified in the Schedule. |
| 2) በአንድ ሰነድ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆነው መብት ወይም ግዴታ ሊተመን የማይችል ከሆነ በዚሁ ሰነድ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን ለእያንዳንዱ ሰነድ በዚሁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተው የቀረጥ መጠን ይሆናል፡፡ | 2) Where the value of the right or obligation executed by means of an instrument can not be determined the amount chargeable on such an instrument is the fixed amount Specified for each Such instrument in the Schedule. |
| 3) አንድ ሰነድ ላይ ተከፋይ የሚሆነው ቀረጥ በብር ሳይሆን በሌላ ገንዘብ ከሆነ የቀረጥ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው የምንዛሪ ልክ ነው፡፡ | 3) Where an instrument is chargeable with stamp duty in respect of any amount expressed in any currency, other than Birr, such amount expressed in any currency, other than Birr, such amount shall be computed on the basis of the prevailing rate of exchange. |
| 4) በስቶክ ወይም በሌላ ዋስትና ባለው ነገር ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ መጠን በዋጋው ላይ ተመስርቶ ከሆነ የቀረጡ መጠን የሚሰላው ሰነዱ በተፈጸመበት ቀን በዋለው አማካይ ዋጋ መሠረት ነው፡፡ | 4) Where an instrument is chargeable with stamp duty on an ad-valorem basis in respect of any stock or of any marketable security, such amount shall be computed on the average value of the stock or security prevailing at the time when the instrument is made. |
| 5) ብዙ የተለያዩ ነገሮች የተጠቃለሉበት ወይም በብዙ ልዩ ሰነዶች የቆመ ማንኛውም ሰነድ በያዛቸው ልዩ ልዩ ሰነዶች መጠን በዚሁ አዋጅ መሠረት በእያንዳንዱ ሰነድ ላይ የሚከፈለው ቀረጥ በመጠቃለል ተደምሮ ይከፈልበታል፡፡ | 5) Any instrument comprising or relating to several distinct matters shall be chargeable with the aggregate amount of duties payable in respect of each separate instrument. |
| 6) በዚህ አንቀጽ ንብረትን በባለቤትነት ለማስመዝገብ በተቋቋመ ሰነድ ላይ የሚከፈል የቴምብር ቀረጥ የሚተመነው፡- | 6) As per this article,the stamp duty payable on documents transferring titles shall be calculated on; |
| ሀ/ በንብረቱ ሰነድ ውስጥ በተወሰነው የንብረቱ ዋጋ ላይ ሆኖ ዋጋው በቢሮው ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ | a/ The price of the property is based on the value specified in the property deed, provided that the |

ነው፡፡

ለ/ ለቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ሲባል በቀረበው የንብረት ሰነድ የንብረት ባለቤትነት የማስተላለፍ የስምምነት ውል ላይ የተመለከተውን ዋጋ የገቢዎች ቢሮ ያልተቀበለው እንደሆነ በታክስ አስተዳር አዋጅ አንቀጽ 4 መሰረት ተገቢው የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት ትክክለኛ የንብረቱ ዋጋ በወቅታዊ የገበያ ዋጋ መነሻ በገቢዎች ቢሮ ይወሰናል፡፡

price is approved by the Bureau.

b/ If the Revenue Bureau does not accept the value specified in the property transfer agreement submitted for the purpose of payment of stamp duty, the actual value of the property for which the appropriate stamp duty is payable shall be determined by the Revenue Bureau based on the current market value, in accordance with Article 4 of the Tax Administration Proclamation.

## 6.የክፍያ ግዴታ

1) በዚህ አንቀጽ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር በአንድ ሰነድ ተጠቃሚ የሆነው ሰው ሰነዱ ላይ የሚተመነውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
2) በኢትዮጵያ ውስጥ ሰነዱን የሚሠራው ወይም የሚሰጠው ሰው ሰነዱ እንደተፈጸመ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ ሆኖም አንድ ሰነድ የተሠራው ወይም የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጭ ከሆነ የቴምብር ቀረጡን የመክፈል ግዴታ ያለበት ሰነዱን ኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ ያስፈጸመ ሰው ነው፡፡
3) የተለየ ስምምነት ከሌለ በስተቀር በኪራይ ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ ያለበት ተከራይ ነው፡፡
4) በመያዣ ሰነድ ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ ተበዳሪው የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
5) በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የቴምብር ቀረጥ ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር የመክፈል ግዴታ ያለበት የንብረት ባለቤትነት የሚመዘገብለት ሰው ይሆናል፡፡

## 6. Liability of Payment

1) Unless otherwise provided in this Article, the beneficiary of a document shall be liable to pay the stamp duty payable on the document.
2) The person who makes or issues a document in Ethiopia shall be liable to pay stamp duty upon the execution of the document. However, if a document is made or issued outside Ethiopia, the person who first executed the document in Ethiopia shall be liable to pay stamp duty.
3) Unless otherwise agreed, the stamp duty in respect of the lease agreement shall be paid by the lessee.
4) The borrower shall be liable for the payment of stamp duty Chargeable on Security deed.
5) The transferee shall unless otherwise agreed be liable for the payment of stamp duty chargeable on documents transferring title to property.

| | |
|---|---|
| 6) ውል ወይም ስምምነት የሚመሰርቱ ወገኖች ለቴምብሩ ቀረጥ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ። | 6) Parties to a contract or to an agreement are jointly and severally liable for the payment of stamp duty thereon. |
| 7) በቅጥር ውል ላይ የሚከፈለውን የቴምብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታ የአሰሪው ነው። | 7) The employer shall be liable for the payment of stamp duty on contracts of employment. |
| 8) ጉዳያቸውን በግልግል የሚያስወስኑ ወገኖች ለቴምብር ቀረጡ አከፋፈል በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ። | 8) Parties to an award are jointly and severally liable for the payment of stamp duty thereon. |
| 9) በህብረት ስምምነት ላይ ለሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ አሰሪውና ሠራተኞቹ በጋራና በተናጠል ተጠያቂ ይሆናሉ። | 9) The employer and employees are jointly and severally liable for the payment of stamp duty on collective agreement. |
| **7. ቀረጡ የሚከፈልበት ጊዜና ሁኔታ** | **7. Time and manner of payment** |
| 1) የቴምብር ቀረጥ የሚከፈልበት ጊዜ፡- | 1/ The stamp duty shall be paid: |
| ሀ/ በመመስረቻና መተዳደሪያ ጽሑፎች ከምዝገባ በፊት ወይም በምዝገባ ጊዜ ፣ | a/ on memorandum and Articles of association, before or at the time of registration; |
| ለ/ በግልግል ውሳኔው ከመሰጠቱ በፊት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ፣ | b/ on awards, before or at the time of issuance of the award; |
| ሐ/ በውል ወይም በስምምነት ሰነዶች ላይ ከመፈረማቸው በፊት ወይም በሚፈረሙበት ጊዜ፣ | c/ on contracts or agreements, before or at the time of signature; |
| መ/ በኪራይ ወይም በተከራይ አከራይ ውል ላይ ውሉ ከመፈጸሙ በፊት ወይም በሚፈጸምበት ጊዜ፣ | d/ on leases, or sub-leases, before or at the time of execution of the contract; |
| ሠ/ በማረጋገጫ ሰነድ ላይ ማረጋገጫ በሚሰጥበት ጊዜ፣ | e/ on notarial acts at the time of issuance; |
| ረ/ በመያዣ ሰነድ ላይ ከመፈረሙ በፊት ወይም በሚፈረምበት ጊዜ፣ | f/ on security deeds, before or at the time of signature; |
| ሰ/ በንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ ሰነድ ላይ የማስመዝገቡ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም በሚፈፀምበት ጊዜ፣ | g/ on documents of title to property, before or at the time issuance is effected; |
| 2) ቴምበር ቀረጥ የሚከፈልበት ሁኔታ | **2) Manner of stamp duty payment** |
| ሀ/ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 በታች በሚሆንበት ጊዜ ክፍያው ተገቢውን ዋጋ የያዘውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈጸማል። | a/ The payment of stamp duty under Birr 50 shall be effected by affixing stamp of appropriate value to the |

ለ/ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ ከብር 50 የበለጠ ሲሆን ወይም የሰነዱ ዓይነትና ሁኔታ ለየት ያለ አሠራርን ሲጠይቅ መስተዳድር ምክር ቤት በሚሠጠው መመሪያ መሠረት ቴምብር ከመለጠፍ በሌላ መንገድ ቀረጡ እንዲከፈል ሲደረግ ይችላል።

3ታዙሀ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 እንደተጠበቀ ሆኖ

ሀ. የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ የሚሠራ ወይም የሚቀበል ሰው በዚህ ቴምብር ሁለተኛ እንዳይሠራ መሰረዝ አለበት።

ለ. ቴምብር የተለጠፈበትን ሰነድ የሚቀበሉ ሰዎች ስለቴምብሩ አሠራር ገቢዎች ቢሮ በሚወስነው መሠረት ይፈጽማሉ።

ሐ. በሰነድ ላይ የተለጠፈ ቴምብር ገቢዎች ቢሮ በሚወስነው መሠረት ካልተሠረዘ ሰነዱ ቴምብር እንዳልተለጠፈበት ይቆጠራል። በዚህ ምክንያት የሚመጣው ኃላፊነት የሚወድቀው በባለጉዳይ ላይ ሳይሆን የቀረጥ ቴምብር በተለጠፈበት ሰነድ በሚሰጠው ወይም በሚቀበል ሰው ላይ ይሆናል።

**8. የገቢዎች ቢሮ ሥልጣንና ተግባር**

ቢሮው፡-

1) በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰነውን ቀረጥ መሰብሰብ እና ይህን አዋጅ የማስፈፀም፤

2) ቀረጥ ከፋዮች ስለቀረጡ አወሳሰን የሚረዱ መዛግብትን፣ ደብተሮችን፣ ወረቀቶችንና ማንኛውንም ልዩ ልዩ ሠነዶችንና ውሣኔዎች እንዲያቀርቡ ለማድረግና ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ያገኘውን ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ራሱ ቀርቦ እንደሚያስመረምር ወይም እንዲያስረዳ የማዘዝ፤

instrument.

b/ when the stamp duty exceeds Birr 50 where the type and nature of instrument so requires, the Executive Council may be directive provide that stamp duty be paid by means other than affixing stamp.

3, Notwithstanding sub Article 1 and 2 of this article;

a/whoever executes or receives an instrument bearing an adhesive stamp shall at the time of execution cancel the same so, that it can not be used again.

b/ persons required to cancel the adhesive stamp cancel it in such manner as will be prescribed by the Regional revenue authority.

c/ Any instrument bearing an adhesive stamp which has not been canceled as prescribed by the revenue authority shall be unstamped. The responsibility arising from the non-cancellation of the stamp shall be on the person executing or receiving the instrument bearing an adhesive stamp and not on the person submitting the document for execution.

**8. Powers and Functions of Revenue Bureau**

The Bureau has the powers and functions;

1) To collect the stamp duty determined under this proclamation, and implement and enforce the provisions of this proclamation ;

2) To order taxpayers to submit records, books, papers, and any other documents and decisions that may be necessary for the determination of their tax liability, and to order the person concerned to personally appear and examine or explain the matter as deemed necessary;

3) ጉዳዩ የሚመለከተው ቀረጥ ከፋይ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ /2/ በተመለከተው መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ሳይሆን በቀረ ጊዜ ቀረጡን በግምት የመወሰንና የመሰብሰብ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

4) ቢሮው ለአገልግሎት ቅልጥፍና የቴምብር ቀረጥ መሰብሰብ በሚያስፈልግባቸው ሴክተሮች የቀረጥ ገቢ የመሰብሰብ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

**9. ቅሬታና ይግባኝ የማቅረብ መብት**

1) ቢሮው በወሰነው የቴምብር ቀረጥ መጠን ላይ የማይስማማ ቀረጥ ከፋይ ቢሮው  ውሣኔውን በጽሑፍ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ በ21 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን በቢሮ ለተደራጀው አቤቱታ አጣሪ  የሥራ ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡

2) አቤቱታ አጣሪ በተሰጠው ውሳኔ ካልተስማማ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 22/2016 መሰረት ለግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

**10.መቀጫን ስለማንሳት**

በቀረጥ ከፋይ ላይ የተጣለን አስተዳደራዊ መቀጫ ቢሮው በተቋሙ የታክስ አስተዳር አዋጅ ፣ ደንብ እና መመሪያ መሰረት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ለማድረግ ይችላል፡፡

**11. ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባዔ ስለሚቀርብ ይግባኝ**

3) to determine by estimation and collect the stamp duty payable under this proclamation if the concerned person failed to comply with its requests provided in sub article /2/ of this article.

4) The Bureau may delegate the collection of tax revenue in sectors where stamp duty collection is required for service efficiency.

9. **Right to file a complaint and appeal**

1) A taxpayer who disagrees with the stamp duty rate determined by the Bureau may submit his complaint to the Complaint Investigation Department within 21 days from the date of the Bureau's written notification of the decision.
2) If a taxpayer disagrees with the decision of Complaint Investigation Department, he may file an appeal with the Tax Appeals Commission in accordance with Tax Administration Proclamation No. 22/2016.

**10.Waiver of  Administrative Fine**

The Bureau may waive, in whole or in part, an administrative fine imposed on a taxpayer in accordance with the Tax Administration's proclamations, regulations, and guidelines.

**11.  Appeals to the Tax Appeal commission**

**1)** Any taxpayer who objects to an assessment of stamp

1) ማንኛውም የቴምብር ቀረጥ ታክስ ስሌት ላይ ቅር የተሰኘ ታክስ ከፋይ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፣
2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የሚቀርብ ይግባኝ፡-
   ሀ/ ቀረጥ ከፋዩ አከራካሪ የሆነውን የቴምብር ቀረጥ መጠን 50 ከመቶ ለቢሮው ካስያዘ፣ እና
   ለ/ የቀረጥ ውሣኔ ማስታወቂያው ወይም በአቤቱታ አጣሪው የተሰጠው ውሣኔ ለታክስ ከፋዩ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ካላቀረበ በግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽኑ ተቀባይነት አይኖረውም።
3) በታክስ አስተዳደር አዋጅ 22/2016 አንቀጽ 57 ላይ ስለ ይግባኝ የተደነገጉት እንደአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሠረት ለሚቀርብ ይግባኝ ተፈፃሚ ይሆናል።

12. **የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ውሣኔን በመቃወም ስለሚቀርብ ይግባኝ**

1) የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ የሰጠው ውሣኔ በሕግ ረገድ ስህተት ነው በማለት ያልተስማማ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን የግብር ይግባኝ ጉባዔው ውሣኔ በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊቀርብ ይችላል፡
2) ይግባኙን ለፍርድ ቤት የሚያቀርብ ይግባኝ ባይ በክርክር ላይ ያለውን የቴምብር ቀረጥ መጠን 75 ከመቶ ለቢሮው ሊከፍል ይገባል፣
3) ይግባኝ የሚቀርበው በህግ ጉዳዮች ላይ ብቻ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሕግ ረገድ ያተነሳውን ክርክር መርምሮ ውሣኔ ሊያጸና ወይም ሊሽር

duty may appeal to the Tax Appeal commission.

**2)** No appeal under sub- article (1) of this Article may be accepted by the Tax Appeal commission unless;

a/ a deposit of 50% of the disputed amount is made to the Bureau ; and

b/ The appeal is lodged within 30 days following the day of receipt of the assessment notice, or the decision of the tax investigation Department.

3) The Provisions of the income tax proclamation No 19/2023 relating to appeal shall, mutatis mutandis, apply to appeals submitted under this proclamation.

12. **Appeals against Decisions of the Tax Appeal commission**.

1) Any party dissatisfied with the decision of the Tax Appeal commission may appeal to the competent court of appeal on the ground that it is erroneous on matter of law within 30 days from the date of receipt of the decision of the Tax Appeal commission.

2) The court of appeal shall hear and determine the question of law arising from the appeal and return the case to the Tax Appeal commission.

3) A party who is dissatisfied with the decision of the appellate court may lodge an appeal to the next court of appeal within 30 days from the date of the decision.

ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጉዳዩን ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባዔው ወይም ለቢሮው ሊመልስ ይችላል፡፡

4) በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ውሣኔው በተሰጠ በ30 ቀን ውስጥ ስልጣን ላለው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

**13. የቴምብር ቀረጥ አለመክፈል የሚያስከትለው ውጤት**

1) ማንኛውም ሠነድ በዚህ አዋጅ መሠረት ትክክለኛ የቴምብር ቀረጥ ካልተከፈለበት በስተቀር በውል ወይም በሕግ ማስረጃ የመቀበል ስልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግሥት መ/ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፣ ምልክት አይደረግበትም ወይም ማረጋገጫ አይሰጥበትም፡፡

2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ1 የተደነገገው በወንጀል ፍርድ ቤት በሚታይ ክርክር በማስረጃነት የሚቀርቡ ሠነዶችን አይመለከትም፡፡

3) በዚህ አዋጅ መሠረት በመረጃነት ተቀባይነት ያላገኙ ሠነዶች ሊከፈልባቸው የሚገባው ቀረጥ በሁለት እጥፍ ተከፍሎባቸው በመረጃነት ሊቀርቡ ይችላል፤ሆኖም ግን በዚህ ሁኔታ የሚከፈለው ቀረጥ ከ 10 ብር ማነስ የለበትም፡፡

4) ከዚህ በላይ በተመለከቱት ንዑስ አንቀፆች የተወሰነው ቅጣት ተፈፃሚ መሆን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 መሠረት ከመክሰስ አያግድም፡፡

4) A party dissatisfied by the decision of the appellate court may appeal to the competent appellate court within 30 days of the decision.

**13. Effect of Non-payment of Stamp Duty**

1) No instrument chargeable with stamp duty shall be admitted in evidence for any purpose by any person having, by law or consent of parties, authority to receive evidence or shall note upon or authenticated by any such person or public office, unless such instrument is duty stamped.
2) The provisions of Sub-Article 1 of this Article do not apply to documents presented as evidence in a criminal court proceeding.
3) Documents that are not accepted as evidence under this Proclamation may be submitted as evidence at double the amount of the tax payable; however, in this case, the tax payable shall not be less than 10 birr.
4) The applicability of the administrative measure specified in the above sub-articles shall not preclude prosecution under Article 15 of this Proclamation.

| | |
|---|---|
| **14. ከቀረጥ ነፃ መሆን**<br>1) የክልሉ መስተዳደር ምክር ቤት በቂ ምክንያት ሲቀርብለት ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊያደርግ ይችላል::<br>2) የአስመጪነት የንግድ ስራ ፈቃድ ያላቸው ነጋዴዎች ለሽያጭ የሚያስመጡት ንብረት በአስመጪዎቹ ስም በሚመዘገብበት ጊዜ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልበትም::<br>3) መንግስት ባጸደቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና ኮንቬንሽኖች መሰረት ሰነዶች ከቴምብር ቀረጥ ነጻ ሊደረጉ ይችላሉ::<br>4) የአክሲዮን ድርሻ የምስክር ወረቀት ሲመዘገብ የቴምብር ቀረጥ አይከፈልም::<br>5) የክልሉ መንግሥት ፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 20/2016 ተፈፃሚ የሚሆንባቸው የመንግሥት መ/ቤቶች ከቴምብር ቀረጥ ክፍያ ነፃ ናቸው። | **14. Exemptions**<br>1) The Regional Executive Council may exempt tax payer from stamp duty upon sufficient justification.<br>2) Stamp duty is not payable when the property imported for sale by traders with an import business license is registered in the name of the importer.<br>3) Documents may be exempt from stamp duty in accordance with international agreements and conventions ratified by the government.<br>4) No stamp duty is payable when registering a share certificate.<br>5) Government offices to which the Regional Government Financial Administration Proclamation No. 20/2016 applies are exempt from paying stamp duty. |
| **፲፭ ቅጣት**<br>1) ማንኛውም ሰው፡-<br>ሀ/ ማናቸውንም ቀረጥ ሊከፈልበት የሚገባውን ሠነድ ተገቢው ቴምብር ሳይለጠፍበት ያስፈፀመ ወይም ከምስክርነት በቀር የፈረመ እንደሆነ፣<br>ለ/ ተገቢውን ቀረጥ እንዳይከፍል ለማድረግ በማሰብ የአንድን ሠነድ እውነተኛ ሁኔታ የደበቀ እንደሆነ፣ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 25 ሺ /ሃያ አምስት ሺ ብር/ በማያንስና ከ35 /ሰላሣ አምስት ሺ ብር/ በማይበልጥ መቀጫና ከ 10 ዓመት በማያንስና ከ 15 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል። | **15/ Penaltiy**<br>1/ Any person;<br>a/ executing or signing otherwise than as a witness documents Chargeable with stamp duty without the same being stamped.<br>b/ Who with intent to defraud the appropriate payment of duty conceals facts bearing on the true nature of any instrument Shall be liable on conviction to a fine not less than Birr 25,000 and not exceeding Birr 35,000 and punished according to the penal law.<br><br>2/ Any person who;<br>a/ If a person is permitted to sell stamps or stamped paper and violates the rules or regulations issued under |

2) ማንኛውም ሰው፤

ሀ/ ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ተፈቅዶለት በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን የጣሰ እንደሆነ ወይም፣

ለ/ ቴምብር ወይም ቴምብር የተለጠፈበት ወረቀት ለመሸጥ ሳይፈቀድለት የሸጠ ወይም ለመሸጥ ያቀረበ እንደሆነ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር 5ሺ. (አምስት ሺ. ብር) በማያንስና ከብር 20ሺ. (ሃያሺ. ብር) በማይበልጥ በገንዘብ መቀጫና ከ5 ዓመት በማያንስና ከ10 ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይቀጣል::

16. **የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በሞትም ሆነ በሌሎች የፍቺ ምክንያቶች መነሻነት የባልና ሚስት የጋራ ሀብት ክፍፍልን ተከትሎ ለባለድርሻዎች ከሚፈፀም የስመ-ንብረት ዝውውር ጋር የተያያዙና አግባብ ላላቸው አካላት ቀርበው በመታየት ላይ ያሉ የቴምብር ቀረጥ አከፋፈል ጉዳዮች በዚህ አዋጅ መሰረት እየተስተናገዱ እልባት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

17.**ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

**18.ደንብና መመሪያ ስለማውጣት**

1) የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ

this Proclamation, or

b/ Whoever sells or offers to sell a stamp or a paper with a stamp affixed thereto without permission shall, upon conviction by a court, be punished with a fine of not less than Birr 5,000 (five thousand Birr) and not more than Birr 20,000 (twenty thousand Birr) and rigorous imprisonment of not less than 5 years and not more than 10 years;

**16.Transitional Provision**

Before the effective date of this Proclamation, stamp duty payment cases related to the transfer of property to the beneficiaries following the division of the joint property of the spouses due to death or other reasons for divorce and which are pending before the appropriate bodies shall be dealt with and resolved in accordance with this Proclamation.

**17. Inapplicable Laws**

Any laws that are inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

**18.Power to issue Regulations & Directives**

1) The Regional Executive Council may issue the necessary regulations to implement this Proclamation.

በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

2) ቢሮው ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**18.አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መንግስት ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አርባ ምንጭ**

**ታህሳስ 5 ቀን 2016 ዓ.ም**

**ጥላሁን ከበደ**

**የደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር**

2) The Bureau may issue directives to help implement this Proclamation and the regulations issued pursuant to this Proclamation.

**18. Effective Date of the proclamation**

This proclamation shall come into force on December 14, 2023, upon its approval by the South Ethiopia Regional State Council.

**Done at Arba Minch December 14, 2023**

**Tilahun Kebede**

**Chief Executive Council of the South Ethiopia Regional State**

## የቴምብር ቀረጥ ታሪፍ ሰንጠረዥ

በሠነዶች ላይ የሚከፈለው የቴምብር ቀረጥ የሚወሰነው፣ የሚጠየቀውና የሚሰበሰበው ከዚህ በታች በተመለከተው ልክ ነው

| ተ.ቁ | የሠነዱ ዓይነት | የተወሰደ ስሌት መሠረት | የማስከፈያ ልክ |
|---|---|---|---|
| ፩ | የማንኛውም የንግድ ሥራ ወይም ከታች በተራ ቁጥር ከተመለከቱት ውጭ የሆነ ማናቸውም ሌላ ማሕበር የተመሠረተበት መተዳደሪያ ደንብ፣<br>ሀ/ መጀመሪያ ሲፈፀም | በቁርጥ<br>በቁርጥ | ብር ፫፻፶<br>ብር ፻ |
| ፪ | የኅብረት ሥራ ማሕበር የብዙሃን ማሕበራት ወይም የሙያ ማሕበራት መተዳደሪያ ደንብ<br>ሀ/ መጀመሪያ ሲፈፀም<br>ለ/ በድጋሚ ሲፈፀም | በቁርጥ<br>በቁርጥ | ብር ፴፭<br>ብር ፲ |
| ፫ | ግልግል | በዋጋው | የሚተመን 1%<br>የማይተመን ብር |
| ፬ | ማገቻ ወይም ቦንድ | በዋጋው | 1% |
| ፭ | የዕቃ ማከማቻ ማረጋገጫ | በዋጋው | 1% |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፮ | ውሎች ፣ስምምነቶችና መግለጫዎቻቸው | በቁርጥ | ብር ፭ |
| ፯ | የመያዣ ሠነድ | በዋጋው | 1% |
| ፰ | የሕብረት ስምምነት<br>ሀ/ ሲመዘገብ<br>ለ/ ሲሻሻል | <br>በቁርጥ<br>በቁርጥ | <br>ብር ፫፻፶ ብር ፶ |
| ፱ | የቅጥር ውል ስምምነት | የአንድ ወር | 1% |
| ፲ | ኪራይ፣ የተከራይ፣ አከራይና መሰል መብት ማስተላለፍ ሠነዶ | በዋጋው | 0.5% |
| ፲፩ | ማረጋገጫ | በቁርጥ | ብር ፭ |
| ፲፪ | የውክልና ስልጣን | በቁርጥ | ብር ፴፭ |
| ፲፫ | የንብረት ባለቤትነት ስም ማስመዝገቢያ | በዋጋው | 2% |

## SCHEDULE OF STAMP DUTY RATES

The stamp duty on each instrument shall be charged leveled and collected at the following rates.

| No. | Instrument chargeable with stamp duty | Basis rates of stamp duty of valuation | Rates of stamp duty |
|---|---|---|---|

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | Memorandum and Articles of association any business organization, of any association<br>a) upon the first execution<br>b) upon any subsequent execution. | Flat<br>Flat | Birr 350<br>Birr 100 |
| 2 | Memorandum and Articles of Association of cooperatives/a/ a)upon 1 execution<br>b) upon any subsequent execution | Flat<br>Flat | Birr 35<br>Birr 10 |
| 3 | Award | On value | a) with de-terminable value 1%<br>b) with undeterminable value Birr 35 |
| 4 | Bonds | On value | 1% |
| 5 | Ware house Bond | On value | 1% |
| 6 | Contracts and agreements and memoranda there of | Flat | Birr 5 |
| 7 | Security Deeds | On value | 1% |
| 8 | Collective agreement<br>a) on 1st execution<br>b) on any subsequent execution | Flat<br>Flat | Birr 350<br>Birr 100 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 9 | Contract of employment | Salary | 1% |
| 10 | Lease including sub-leases and transfer thee of | On value | 0.5% |
| 11 | Not Anal act | Flat | Birr 5 |
| 12 | Power of Attomey | Flat | Birr 35 |
| 13 | Register title to property | On value | 2% |